# አባቱን ማየት የጓጓ ልጅ ካለቀኑ ይወለዳል።

ተኮላ መኮንን
TEKOLA MEKONEN
tekolamekonen@yahoo.com

ባለፈው ሳምንት በዳላስ ተደርጎ የነበረው የልማት ስብሰባ ከተጠበቀው በላይ ውጤታማ ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ ከ 500 በላይ የሚሆን የዳላስ ነዋሪ ሕዝብ የተገኘ ሲሆን በእንግድነት የመጡት ተወካዮች የተላኩበትን መልእክት ለተሰብሳቢው ለማስተላለፍም እድል አግኝተዋል። በተሰብሳቢው ጨዋነት ሁሉም የተደሰተ ቢሆንም ጥያቄ አለን ብለው በመነሳት ጥያቄ ሳይሆን ተራ ስድብ ይሳደቡ የነበሩትንም ለመመልከት እድል አጋጥሞናል። በስድብ የፈራረሰ መንግስት ሰምተን ባናውቅም፡ ስድብን እንደ መታገያ መርህ አድርገው የሚቆጥሩ ሁሉ ድክመታቸውን እንጂ ጥንካሬአቸውን እንደማያሳይ ቢያውቁ ኖሮ ከድርጊታቸው ይቆጠቡ ነበር ብለን እናምናለን። በዘር ላይ ያነጣጠረ ስድብ እየተሳደቡ መንግሥት ዘረኛ ነው ብሎ እንዴት መውቀስ ይቻላል። ዓባይን እኛ ስልጣን ስንይዝ እንገነባዋለን ማለትስ እኔ ካላደረኩት ትክክል አይደለም ማለት አያስመልስንምን? ግብጾች ግድቡ እንዲገነባ ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስን ቀደም ሲል አነጋግረዋል የሚሉን ያካባቢያችን ፖለቲከኞች ከማውራታቸው በፊት ሁለት ጊዜ ቢያስቡ መልካም ነበር። ለምን ቢሉ ውሸት ሲበዛ እውነትን ያዳክማልና። ደግሞ አዳማጭም አዳምጦ አዳምጦ ትዝብት ላይ መውደቅ እንደሚመጣም መገንዘብ የፓለቲከኛ ይቅርና የማንም ግለሰብ ግንዛቤ መሆን ይኖርበታል። ስለዚህ ስላለፈው ስብሰባ በሰፊው ሰሞኑን እንደምተርክ ቃል በመግባት ዛሬ ስለተነሳሁበት ነጥብ ላተኩር።

"ዝም ባለ አፍ ዝምብ አይገባበትም" በማለት ከሚገባው በላይ በትእግስት መቆየቴ እሙን ነው። ከሁሉም በላይ ግለሰቦችን እንደ ድርጅት ቆጥሮ አላስወጣም አላስገባም የሚል የመንግሥት ተቃዋሚ ድርጅት ነኝ ባይ ስብስብ መገንዘብ ያለበት ነገር ቢኖር ግለሰቦችን በመሳደቡ በስልጣን ላይ ያለ መንግሥት ነገ በኔ ብሎ በመፍራት ስልጣኑን ኑና ተረከቡኝ እንደማይል ነው። የመቃወም መብት አለኝ ብሎ የሚታገልን ስብስብ ማክበሬን ስናገር ይህ አክብሮቴ ግን የመደገፍ መብት መኖሩን እስከተቀበሉ ድረስ መሆን እንዳለበት መረዳት ይኖርባቸዋል። ግለሰብ ሆኜ ሳለ የተቃዋሚ ድርጅት ነን ባዮች የስድብ ውርጅብኝ ሲያወረዱብኝ ሳይ ሳላውቀው የሠራሁት ትልቅ ሥራ እንዳለ ገባኝ። ይኸውም በውሸት ዓለም ተተብትበው መውጫ ማጣታቸውን መገንዘቤ መሆኑ ነው። በዚህ በዳላስ ከተማ ነዋሪ ከሆንኩ ደግሞ ውሎ አደረ።

በተለየየ ብሎግና ድሕረ ገጽ የሚሳደቡት አቶ መንግስቱ ሙሴና ጓዶቻቸው ከጊዜ ይማሩ ይሆናል ብዩ ትቻቸው ነበር። አንድ ጓደኛዬ ምእራብያውያን IF YOU HAVE AN ISSUE HAMMER THE ISSUE, IF YOU HAVE A POINT HAMMER THE POINT IF YOU HAVE NETHER HAMMER THE TABEL ይላሉ ይለኝ ነበር። አቶ መንግስቱና መሰል የዳላስ ደጋፊዎቻቸው ግን አህያውን እየፈሩ ዳውላ መደብደባቸውን ቀጠሉበት። ዛሬ የቀራቸው ነገር ቢኖር ሁሉን ነገር መቃወም፡ ሁሉን ግለሰብ መዝለፍ፡ እኛ የማንደግፈው ምንም ሃሳብ መኖር የለበትም የሚል ነው። ዝም ካላላችሁ የስድብ ውርጅብኝ ይወርድባችኋል፡ ከእድር እናባርራችኋለን፣ ካገር እናስወጣችኋለን አልፈው ተርፈው እሳቸው ሥጋወ ደሙ ተቀብለውም እሳደባለሁ ፖለቲካውን እመራዋለሁ እያሉ እናንተ ግን መናገርም አትችሉ ቤተክርስቲያንም አትደርሱም በማለታቸው የመብት ጉዳይ ሆነና በሕግ መብትን ለማስከበር ክስ

እንዲመሰረት ግዴታ ሆነ። ይህንን ለመጥቀስ የወደድኩት አቶ መንግስቱና ደጋፊዎቻቸውን ምን ያህል እየታገስኩ እንዳለሁ ለመግለጽ ያክል ነው። ዘረኛነትን እቃወማለሁ የሚሉት አቶ መንግስቱና ተከታዮቻቸው ዘረኛ ለመሆናቸው እስከዛሬ የሚጽፉትን ማንበቡ በቂ ነው። ኧረ ትግሬ ጠላታችን ነው ብለው አይናገሩ ሲባሉ እኔ ዘረኛ አይደለሁም ልጄን ለትግሬ ድሬአለሁ ይሉናል።

በፖለቲካው ቢለዩም የልማት ሥራው እንዲቀጥል ይተባበሩ ሲባሉ ለግላቸው ማልማቱን ተስማምተው ደፋ ቀና እያሉ ሌላውን ግን አትሳተፍ ብለው አምርረው ይናገራሉ። ለዚህም ነበር አምባሳደር ታዬ እርሶ ባህር ዳርና አዲስ አበባ እንደሚያደርጉት ሁሉ ሌላውም ቢያደርገው ለምን ይቃወማሉ? ብለዋቸው የነበረው። አቶ መንግሥቱ ሙሴ የግለሰቦችን ስም እያነሱ በድኅማ የሚኖሩ ናቸው በማለት ድህነትን እንደ ወንጀል ሲተርኩልን ከርመዋል። ለነገሩ በድኅማ ይኖራል ካሉት አንዱ ግለሰብ እኔ ነኝና ለመረጃ ያክል እኔው ልመልስላቸው። እኔ በድኅማ ከመንግሥት ገንዘብ ተቀብዬም እንደማላውቅ ልነገራቸውና ጥርጣሪያቸውን ላውርድላቸው። ለውይይት ያክል ግን አይደለም እንጂ ቢሆን እንኳን ድርጅታቸው “ለድሃ መብት የሚታገል ድህነትን ለማጥፋት የሚታገል ነው” እያሉ እንዴት ድህነትን እንደ ወንጀል ሊነግሩን ይነሳሉ። እሳቸው PARKING እየሰሩ ያካበቱት ንብረት አላቸው ብሎ ያልተናገረን ግለሰብ ለምን በድህነቱ ያፌዛሉ። ሻትል እየነዳሁ ልጆቼን ማሳደጌ እውነት ሆኖ እያለ ለምን ከሻትል መንዳት ያልወጣ ግለሰብ ብለው የሥራን ክቡርነት ያጥላላሉ። እኔ እሳቸው የቆመ መኪና ጠባቂ ነበሩ ብዬ አላውቅምና እሳቸውም በልዩነት ሃሳብ ላይ ቢያተኩሩ እንጂ የኔ ሾፋሪ መሆን የሳሸው መኪና ማገድ ለሃገራችን እድገት የሚያመጣው ለውጥ እንደሌለ እንስማማ። ካቲካላ የሚቸረችር ፖለቲከኛ ሳይ ደግሞ ሁል ጊዜ ያስገርመኛል።

አቶ መንግሥቱ አሁንም ወደ ትግላቸውና ንግዳቸው ፊታቸውን ቢዞሩና እኔን ለቀቅ ቢያደርጉኝ መልካም ነው። ካልሆነ አባትና እናቱን ገድሎ ወላጅ የለኝም ብሎ እንደሚያለቅስ ወጣት ይሆናሉ ብዬ እፈራለሁ።